# ማመልከቻ ለክቡራን ኢትዮጵያውያን

አየለ ታደሰ (ዶ/ር) [1]

## 1) "ስልጣንን ከመንግስት ወደ ሕዝቡ የማውረድ ልማድ"

**መግቢያ**

የዚህን ጽሁፍ "ማመልከቻ ለክቡራን ኢትዮጵያውያን" የተባለውን አርዕስት የተዋስኩት በየካቲት 1966 እንቅስቃሴ ወቅት ኢትዮጵያውያን እንዲያደምጡት ከወጣ የአንድ ዘፈን አርዕስት ነው። በዚያን ወቅት ናዝሬት በሚገኘው የአፄ ገላውዴዎስ አንደኛ ደረጃ ተማሪ ነበርኩ።

በዛሬውም ጊዜ አድማጭ ከተገኘ እኔም የ"ማመልከቻ ለክቡራን ኢትዮጵያውያን" የማስታወሻ ደውልን ለውይይት በር ከፋች እንዲሆን "ቁጥር 1 - ስልጣንን ከመንግስት ወደ ሕዝቡ የማውረድ ልማድ" የሚለውን ፅሁፍ "ለኢትዮጵያ ሕዝብ" ጀባ እላለሁ። ቁጥር 2 ና 3 በይደር ይቆየን።

በተጨማሪም ይህንን ፅሁፍ "አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የ8ተኛው "ራዕይ ለኢትዮጵያ" ወይም "ቪዥን ኢትዮጵያ" ላይ በሌላ አርዕስት ስም ቀርቦ እንደነበር ለማስታወስ እወዳለሁ።

ፅሁፉ የሚያተኩረው የምስራቅ አውሮፓውያን "ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ[2] ወደ ምዕራቡ ዲሞክራሲ[3]" እንዴት እንደተሸጋገሩ ይዳስሳል። አዲስ የምርጫ ቦርድ እንዳዋቀሩና ከዚህም ተከትሎ ትክክለኛው የአመራረጥ ተሞክሮና የፖለቲካ ልምድ ለአገራችን በሚስማማ መልኩ በምን ዓይነት ሁኔታ ልንጠቀምበት እንችላለን? በሚለው ዙሪያ ያውጠነጥናል።

ሌሎች የምስራቅ አውሮፓም አገራቶች (እንደ ቼኮዝሎቫኪያ፣ ም/ጀርመን) ሆነ የደቡብ አፍሪካ[4] የፖለቲካ ለውጦች ከሃንጋሪያውያን የፖለቲካ ለውጥ ልምድ መማራቸው ታሪክ ይመሰክራል። ከዚህም በተጨማሪ ይህ የምስራቅ አውሮፓውያን ለውጥ በሚካሄድበት ወቅት ሃንጋሪ ውስጥ ተማሪ ስለነበርኩ የተደረገውን ለውጥ በዓይኔ አይቻለሁ። እንዲያውም ቡዳፔሽት (የሃንጋሪ ዋና ከተማ) ውስጥ በሚገኘው የአንድ የኦዲቲንግ ድርጅት ውስጥ እየሰራሁ ስለነበር በተዘዋዋሪ መንገድም ቢሆን መንግስታዊ የሆኑ ድርጅቶች ወደ ግል በሚዛወሩበት ሁኔታ ላይም ተሳትፌያለሁ።

ይህንን መጣጥፍ ለናንተ ሳቀርበውም እንደ "ግብዝነት" ሳይሆን እንደ "ታናሽ ወንድም" የማውቀውን እዚህ ግባ የማትባለውን እውቀቴን ለማካፈል እና ከስህተቴም ለመማር የአንባቢውንም አስተያየት እንደማከብር በማስታወስና በታላቅ አክብሮት ነው።

## የምስራቅ አውሮፓ የፖለቲካ ለውጥ

አንዳንድ ጊዜ ውጭ አገር የማያቸው የፖለቲካ ለውጦች እና ድርጊቶች "ምነው አገሬ ውስጥ እንዲህ በሆነ" የምላቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ "በሰላም" ማለትም ያለምንም ደም መፍሰስ የፖለቲካ ለውጥ ማድረግ ነው።

የምስራቅ አውሮፓውያን ከ"አብዮታዊ ዲሞክራሲ ወደ ምዕራቡ ዲሞክራሲ" የተደረገው የፖለቲካ ለውጥ (Reform) ሪፎርም እንጂ ሪቮሉሽን "አብዮታዊ" አልነበረም። የፖለቲካ ለውጡ "አብዮታዊ" እንዳልሆነ ታሪክ ስለሚመሰክር እዚህ ላይ ነጥቦችን ማቅረቡ አስፈላጊ አይመስለኝም።

አሁን አገራችን ውስጥ ከ107-108 በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይገኛሉ ይባላል። በእኔ አስተያየት እንዲያውም የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲበዙና እንዲበራከቱ መበረታታት ይኖርበታል። ለ100 ሚሊየን ህዝብ ከ250 - 300 የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢፈጠሩ እንኳን ማስተናገድ የሚቻልበት አቅምና ችሎታ ብሎም አራት (4) ወይም አምስት (5) የፖለቲካ ፓርቲዎች በመምረጥ ወደ ፓርላማ ማስገባት ይቻላል የሚል እምነት አለኝ። እንዴት ሊሆን ይችላል?

መጀመሪያ የምስራቅ አውሮፓ የፖለቲካ ለውጥ (Reform) የተካሄደባት አገር ፖላንድ ነበረች። የመጀመሪያ ዲሞክራሲያዊ ምርጫም ተደርጎ ወደ ሃያ ዘጠኝ (29) የሚደርሱ ፓርቲዎች ወደ ፓርላማ ገቡ።

በ1989 ዓ.ም. የሃንጋሪ የህዝብ ብዛት 10 ሚሊየን ነበር። ከ"አብዮታዊ ዲሞክራሲ ወደ ምዕራቡ ዲሞክራሲ" ሰላማዊ የፖለቲካ ሽግግር ለማድረግ የተጠቀሙበት መንገድ እና በተጨማሪም ከስልሳ አምስት (65) የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ስድስቱ (6) ብቻ ወደ ፓርላማ የገቡበትን ሚስጥር ማወቁ ተገቢ ይመስለኛል።

ስለሆነም ሃንጋሪ[5] ከፖላንድ የምርጫ ውጤት በመማር ከ"አብዮታዊ ዲሞክራሲ ወደ ምዕራቡ ዲሞክራሲ" ለማድረግ የለውጥ ጎዳናን ተከተለች። ለዚህ የፖለቲካ ለውጥ መነሻ የነበረው፤

1) ካዳር ያኖሽ የሃንጋሪ ኮሚኒስት መሪ ሆኖ የአገሪቱ መንበረ ስልጣኑን በመያዝ ይመራ ነበር።
2) ሃንጋሪ $21.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር[6] ዕዳ ውስጥ ተነክራ ነበር።
3) ሃንጋሪ ውስጥ 13 የሚሆን ዘውጎች ነበሩ[7]።

በፖለቲካ ለውጡ ወቅት (1989) የነበረው የሃንጋሪ ሁኔታና በአሁኑ ወቅት (2018 - 2019) ያለው የኢትዮጵያ ሁኔታ ብዙ የሚያመሳስላቸው ነገሮች አሉ። ከነዚህም ከሚያመሳስላቸው ነገሮች ውስጥ፤

1) የለውጡ እንቅስቃሴ እንደተጀመረ ወዲያውኑ ውጪ አገር የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተቃዋሚዎች ወደ አገር ውስጥ መግባታቸው።

2) የፖለቲካ ፓርቲዎች ከገቡም በኋላ እርስ በርሳቸው መናቆራቸውና አንድ ስምምነት ላይ ሊመጡ አለመቻላቸው።

3) አንዳንዱ ጣቱን መንግስት ላይ መቀሰር መጀመሩ። እንዲሁም "እኛ"ና "እነሱ" የሚለው ሃሳብ በግልፅ መጀመሩ።

> አንዳንዱ የፓርቲ መሪዎች "እኛ እድሚያችንን በሙሉ በትግል ስላሳለፍን ይህ ውጤት የኛ ውጤት ነው።" ስለዚህ እኛ ደግሞ የበትረ-ስልጣኑ ተረኞች ነን አሉ።
>
> ሌላኛው ፓርቲ "እናንተ እስካሁን የገዛችሁት ይበቃል። ስለሆነም እኛ በስደት የምንገኝ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስለሆንን እና ህዝቡ የምርጫ ዕድሉን ከሰጣችሁት እንደምንረታችሁ እርግጠኞች ነን" አሉ።
>
> የተቀሩት ደግሞ እኛ የተዘጋጀነው የዚህን አካባቢ ህዝብ ገንጥለን ለመውሰድ ነው። እና መድረኩን ስጡንና እናሳያቹሃለን አሉ።

የፖለቲካ መሪዎችና ፖለቲከኞች አገሪቷ ቀውጢ ውስጥ እንድትገባ አደረጓት። የሃንጋሪ ህዝቡ የፖለቲካውን ትዕይንት በማየት

- ከፊሉ "እንኳን መጣችሁልን" ይላል፤
- ከፊሉ ደግሞ እረ "አገራችንን ሊያተረማምሷት ነው" በማለት ስጋታቸውን ይገልጻል፤
- ከፊሉ ደግሞ ምንም "መፍትሄ የሌለው እንዴ ምን ጉድ መጣብን? ወደ ነበረው ወደ ካዳር ያኖሸ የሶሻሊስት ስርዓት መመለስ አለብን" እያለ ሃሳቡ ያቀርባሉ።

መንግስት የጊዜው ሁኔታ በጣም አስፈራው። ስለዚህ መንግስት አንድ ዘዴ ዘየደና የሚከተለውን ኃሳብ አቀረበ፤

> <u>የሶሻሊስት ፓርላሜንቱ</u> <u>የ"ዲሞክራሲ ጥቅል"</u>ን እንዲያሳልፍ፤ ከዚያም ፓርላሜንቱ <u>ራሱን በ"ዲሞክራሲ ጥቅል" ውሳኔ ውስጥ እንዲያከስም፤</u> ጊዜያዊ የሽግግር መንግስት ተመስርቶ አንድ ጠ/ሚር ቦታውን እንዲይዝ፤ <u>በጠረጴዛ ዙሪያ የሚደረግ ውይይት መጀመር እንዳለበት፤</u> ከህዝቡ ተወካዮች ተመርጠው / ተወክለው የአገሬው ነዋሪ በምን ዓይነት የአስተዳደር ስርዓት መመራት እንደሚፈልግ እንዲያወያዩ፤ <u>ተወካዮቹ የራሳቸውን ጊዜያዊ መዋቅር</u> እንዲመሰርቱና <u>ከስድስት እስከ ዘጠኝ ወራት</u> በሚሆን ጊዜ ውስጥ ስራቸውን እንዲያከናውኑ ውጥን አወጣ።

በዚህም መሰረት በ1989 ላይ <u>573</u> የህዝቡን ተወካዮች ከእያንዳንዱ አካባቢ በማስመረጥ በወቅቱ የነበረው <u>የሶሻሊስቱ የምርጫ ቦርድ የመጨረሻ ስራውን በዚህ መልክ አጠናቀቀ።</u>

573ቱ የህዝብ ተወካዮቹ <u>በሶስት ንዑሳን</u> ደረጃ ተከፍለው ስራቸውን ማፋጠን ተያያዙ።

1) **<u>ህገ-መንግስት</u> ማርቀቅ**፤ -
   በተለይም የግለሰብን መብት የሚጠብቅ - አዲስ ህገ መንግስት ማርቀቅና ብሎም በረቂቁ ላይ ህዝቡንም ማወያየት፤

2) **<u>የምጣኔ ሃብት ፖሊሲ</u> መንደፍ** -
አገሪቷ የነበረባትን ዕዳ እንዴት መክፈል ይገባታል? እና በወቅቱ የነበረውን የምጣኔ ሃብቱን የሚያረጋጋ ፖሊሲ መቀየስ፣ የዳቦ ዋጋ እንዳይንር ፖሊሲ መቀየስ፣ የውጭ አገር ብድርን በተመለከተ ከኢትዮጵያ የሚለየው ሃንጋሪ ብድሩን ስትበደር ሙሉ ለሙሉ ለአገሪቷ ልማት ላይ ውሏል።

3) **<u>የፖለቲካ መድረኩ</u>** የያዙት ደግሞ መድረኩን ማስፋትና የነፃ ምርጫ መዋቅር መዘርጋት ነበር።
የምርጫ ቦርድ ማጠናከርና የምርጫ ህግን ማርቀቅና አዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንዲፈጠሩ ማበረታታት።

**<u>በቁጥር 3 - የፖለቲካ መድረኩ ላይ ላተኩር።- በተለይም የምርጫ ህግ በተመለከተ</u>**

573ቱ የሃንጋሪ ህዝብ ተወካዮች በአገር ውስጥ ያሉትና ከውጪ አገር ለገቡት የፖለቲካ ፓርቲዎች ተቃዋሚዎች የሚከተለውን ሃሳብ አቀረቡ።

1) "ወደ ህዝቡ እንዲወርዱ"ና የዲሞክራሲ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ፣
2) እንደ አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ እንዲመዘገቡ፣ ለመመዝገብ ደግሞ <u>የአባላቶች ፊርማ</u> እንዲያሰባስቡና፣
3) <u>የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን</u> እንዲያሳውቁ መመሪያ ወጣ።
4) የምርጫ ቦርድም ይህንን ለሚያሟሉና የአባላቶቹን ስምና አድራሻ ካጣራ በኃላ ለመወዳደር የሚያበቃቸውን ጊዜያዊ የእውቅና ሰርተፊኬት ለፖለቲካ ፓርቲዎች እንደሚያዘጋጅ አስታወቀ።

<u>ቀደም ብለው በትግል ላይ የቆዩና</u> <u>አገሪቷን ለመገንጠል ያለሙ ግለሰቦችና የፖለቲካ ፓርቲዎች</u> ወደ ታች የመውረዱ ነገር ባይዋጥላቸውም የመንግስት "ህግ" ነውና እንደ አዲስ ፓርቲ ለመመዝገብ ወደ ታች መውረዱን ተያያዙት።

መንግስትም በመካከል በመግባት የፖለቲካ ፓርቲ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማስረዳት የፖለቲካ ሀ ሁ ማስተማር ጀመረ።

<u>የፖለቲካ ፓርቲ</u>[8] <u>ማለት አንድ አይነት አመለካከት ያላቸው ግለሰቦች ተሰባስበው፣ እንደ አንድ ግለሰብ ሆነው ሲሰሩ፣ ለሚያቋቋሙት ድርጅት የፖለቲካ ፕሮግራም ቀርፀው ሲንቀሳቀሱ ነው። የፖለቲካ ፕሮግራሙ የሚያጠቃልለው "... በአስተዳደር፣ በምጣኔ ሃብት፣ በእርሻ፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በእንዱስትሪ፣ በንግዱ፣ በመገናኛ ዘርፍ፡ ወዘተ" ፓርቲው ያለውን አቋም የማሳየት ግዴታ ይኖርበታል።</u>
<u>ለአጠቃላይ ህዝብ አስተሳሰባቸውን ወይም ፍልስፍናቸውን አስረድተው፣ ከሌላ ተመሳሳይ የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ተፎካክረው፣ በህዝብ ተመርጠው ወይም የአብዛኛው ህዝብ የምርጫ ካርድ አግኝተው፣ የመንግሥቱን አስተዳደር ለተወሰነ ጊዜ ለመምራት የሚችል ድርጅት ነው።</u>

ከውጪ አገራት የመጡትን ፓርቲዎች ጨምሮ ስልሳ አምስት (65) የፖለቲካ ፓርቲዎች ተመዘገቡ። በእጩነት ለመመዝገብ የፖለቲካ ፕሮግራምና የተወሰኑ አባላቶች ፊርማ ማሰባሰቡ አስፈላጊ ነበር። ከነዚህም ከ65 ፓርቲዎች ውስጥ 90% የሚሆኑት አዳዲስ የተመሰረቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው።

መንግስትና አዲሱ የምርጫ ቦርድ ሶስት የምርጫ ውድድር እርከኖችን አዘጋጁ።

1) የአካባቢ፤
2) የአውራጃና
3) የክፍል አገር።

እንግዲህ በምሳሌ ላስረዳ፤




በመጀመሪያ ዙር የአካባቢ የምርጫ ውድድር ከተመዘገቡት ስልሳ አምስት (65) ፓርቲዎች ውስጥ ያለፉት 30 የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው። ከ30% በላይ ያመጡት በቀጥታ ለሚቀጥለው ደረጃ ሲያልፉ 25% ያመጡት ደግሞ 30% እንዲሞላላቸው ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተዋሃዱ። እዚህ ደረጃ ላይ ውህደቱ የፖለቲካ ፕሮግራማቸውንም ያጠቃልላል።




በሁለተኛው ዙር የአውራጃ ምርጫ ውድድር ያለፉት 12 የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው። ከ30% በላይ ያመጡት በቀጥታ ለሚቀጥለው ደረጃ ሲያልፉ 25% ያመጡት ደግሞ 30% እንዲሞላላቸው ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተዋሃዱ።

በሶስተኛው ዙር የክፍለ ሃገር ምርጫ ውድድር ያለፉትና ፓርላሜንት ውስጥ የገቡት ስድስት (6) የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው።

በአጠቃላይ ከስልሳ አምስት (65) የፖለቲካ ፓርቲዎች ስድስቱ (6) የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዴት ወደ ፓርላማ እንደገቡ ከላይ አይተናል።

## እንግዲህ እኛ ኢትዮጵያውን ከዚህ ሁኔታ ምን እንማራለን?

የግል ምልከታዬን ለውይይት በሚሆን መልኩ እንዲህ ላቅርብ።
አሁን ባለው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ፤

1) የአገራችን ፖለቲካ በሽግግር ላይ ስላለች - በቲም ለማና ጠ/ሚ ዶ/ር አቢይ የሚመራው መንግስት ቀና መንገድ ይዟል።
2) የህገ-መንግስት ፖሊሲ እና የምጣኔ ሃብት ፖሊሲ ግን ምንም ለውጥ አይታይበትም። በገጠሩም ሆነ በከተማው ኑሮው እጅግ ከባድና ከገቢው ጋር ተመጣጣኝ አይደለም።
   ሀ) የህገ መንግስቱ ፖሊሲ የመለወጡ ስራ በአሁኑ ጊዜ መለወጥ አንገብጋቢ ስራ ስለሆነ ከሃንጋሪው የፖለቲካ ለውጥ መንገድ ብዙ ልንማር እንችላለን የሚል አሳብ አለኝ።
   ለ) በተጨማሪም ኢትዮጵያ በውጭ አገራት ዕዳ ጫና ውስጥ ተዘፍቃ ትገኛለች። ኢትዮጵያ ብድሩን ስትበደር አብዛኛውን የመጣው ብድር በወያኔ ባለስልጣኖች መዘረፉ ልዩ ያደርገዋል። ስለዚህ ከብድሩ ውስጥ ስንት እጅ (%) ነው በልማት ላይ የዋለው? ምን ያህል ባለስልጣኖች ዘረፉት? የተዘረፈው ገንዘብ የት ነው የተቀመጠው? ምን ያህል እጅ (%) ንፁህ ብድር (ከተዘረፈው ውጪ) ኢትዮጵያ አለባት? የሚል ጥናት ከሁሉ አስቀድሞ መደረግ ይኖርበታል። ይህ ተግባር አሁን በስልጣን ላይ ያለው የዶ/ር አቢይ አህመድ እንደ ሽግግር መንግስት ኃላፊነቱን በመውሰድ በጥናት መልክ ሊያቀርበው የሚገባው ይመስለኛል። ምክንያቱም መረጃው እጁ ላይ ስላለ ለሕዝቡ ግልፅ የማድረግ ግዴታ ያለበት ይመስለኛል።
3) የሰላም መደፍረስና ህዝቡ ከሚኖሩባቸው ቀያቸው መፈናቀል በአገሪቱ ውስጥ ይታያል።
4) አገራችን በቋንቋ ክልል የተዋቀረች ስለሆነችና አንደኛው ክልል ህብረ-ብሔራዊ ለሆኑ ፖለቲከኞችና የተወሰኑ ወጣቶች "እስቲ እዚህ አካባቢ ትደርሱና" የሚል አዝማሚያ በመኖሩ።
5) ሰላም መፍጠር የመንግስት ተቀዳሚ ተግባር በመሆኑ ኢትዮጵያውያንን የሚጠቀልል ወታደር ማዘጋጀት እዚህ ላይ ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል።

እንግዲህ ሰላም ከተፈጠረ በኋላ የኢትዮጵያ መንግስት እና ምርጫ ቦርድ ምን ማድረግ እንደሚችል እዚህ ላይ ልጠቁም።

> የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ለአንድ ጊዜ ብቻ አካባቢያዊ፤ ክፍለ አገራዊ እና አገራዊ ምርጫን ለማድረግ - የ3 ዙር ምርጫ አሁን ካለው ህገ መንግስታዊ ክልሎች ውጭ በራሱ የሆነ አገራዊ የምርጫ ንድፍ ሊኖረው ይገባል። ይህ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ህብረ-ብሔራዊ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወደ ስልጣን መሰላል እንዲወጡና አዳዲስና የተደበቁ የፖለቲካ መሪዎችን ወደ መድረክ እንዲመጡ ስለሚያስችል ነው።

ወደ አገር ቤት ለገቡትና እንደ አዲስ ለሚፈጠሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ መንግስት / ምርጫ ቦርድ የሚከተለውን ሃሳብ እንዲያቀርብ ቢደረግ መልካም ይመስለኛል።

1) "ወደ ህዝቡ እንዲወርዱ"ና የዲሞክራሲ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ፤
2) እንደ አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ እንዲመዘገቡ፤ ለመመዝገብ ደግሞ የአባላቶች ፊርማ እንዲያሰባስቡ፤ የቄሮና የገርማ ወይም የሌሎች የወጣቶች እንቅስቃሴ በተጠሪነት፤ በተጠያቂነትና በኃላፊነት እንዲመሩ ያስችላል።
3) የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን እንዲያሳውቁ መመሪያ ማውጣት።
   የፖለቲካ ፕሮግራሙ የሚያጠቃልለው "… በአስተዳደር፤ በምጣኔ ሃብት፤ በእርሻ፤ በትምህርት፤ በጤና፤ በእንዱስትሪ፤ በንግዱ፤ በመገናኛ ዘርፍ፡ ወዘተ" ፓርቲው ያለውን አቋም የማሳየት ግዴታ ይኖርበታል።
4) ቋንቋን፤ ሃይማኖትንና ዘውግን መሰረት ያደረገ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዳይቋቋሙ በህግ ማገድ።
5) ማንኛውም ግለሰብ በፖለቲካ ወይም ማሕበረቡ በሚፈቅድለት መንገድ እንዲደራጅ ግን በመዋቅር ውስጥ ሃላፊነት ለመውሰድ የሚያስችል ሁኔታን ማዘጋጀት።

አሁንም የምርጫ ንድፉን በምሳሌ እንዳስረዳ ይፈቀድልኝ። አሁንም በድጋሚ ይህ የኢትዮጵያ የአመራረጥ ንድፍ ለውይይት የቀረበ መሆኑን እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ።

## የወረዳዎች ምርጫ

በ2015 ምርጫ 43 500 የምርጫ ጣቢያዎች ነበሩ። ነገር ግን ለሂሳብ እንዲመቸኝ 40 ሺህ የሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች አሉ እንበል። የምርጫ ጣቢያዎች በቀይ ነጠብጣብ ይመሰላሉ። አሁን ባለው የምርጫ ህግ መሰረት በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ 1000 መራጮች ይኖራሉ። ስለዚህ በአጠቃላይ 40 ሚሊየን መራጭ ህዝብ አለ ማለት ነው።






አንድ ወረዳ ውስጥ 50 የምርጫ ጣቢያዎች አሉ እንበል። በአንድ ወረዳ ውስጥ በአማካይ 3 የፖለቲካ ፓርቲዎች ይወዳደሩ እንበል። ወረዳዎች በአራት ማዕዘን ይመስላሉ። በአጠቃላይ 800 ወረዳዎች ይኖራሉ። ስለሆነም በምርጫ ውጤት 30% ያመጣ በቀጥታ ያልፋል። 800 ወረዳዎች የሚያርፉት አሁን ባለው "ክልል" መዋቅር ውስጥ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል።

በመጀመሪያ ዙር ምርጫ - ባጠቃላይ ከ250-300 የፖለቲካ ፓርቲዎች ይመዘገቡ እንበል። ከ25-29% ያገኙት ከሌሎች ጋር በመዋሃድ ለሚቀጥለው ምርጫ ይዘጋጃሉ። ስለሆነም ከ90-110 የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሁለተኛ ዙር ምርጫ ይዘጋጃሉ።

**የአውራጃዎች ምርጫ**

አንድ አውራጃ ውስጥ 1 ሚሊየን መራጭ ወይም 1000 የምርጫ ጣቢያዎች አሉ እንበል። በአንድ አውራጃ ውስጥ በአማካይ 3 ወይም 4 የፖለቲካ ፓርቲዎች ይወዳደሩ እንበል። አውራጃዎች በእንቁላል ወይም አራት ማዕዘን ቅርፅ ይመሰላሉ። በዚህ ደረጃ ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ነጥቡን ለመሙላት ሙሉ በሙሉ መዋሃድ ይችላሉ። የፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸው አማራጭም ሁለት ነው። መዋሃድ ወይም ከጨዋታው ሜዳ መውጣት። በአጠቃላይ አርባ (40) አውራጃዎች ይኖራሉ። በአርባውም አውራጃዎች ምርጫ ይካሄዳል።







አርባ (40) አውራጃዎች የሚያርፉት ቦታዎች አሁን ባለው አንድ "ክልል" ውስጥ ብቻ መሆን አይገባውም። ማለትም ለምሳሌ የኦሮምያ "ክልል" ከሚዋሰኑት "ክልሎች" ጋር በሰሜንም፣ በምስራቅም፣ በደቡብም፣ በምዕራቡም ማዛመድ ያስፈልጋል። 1000 የምርጫ ጣቢያዎችን በሁለት ወይም በሶስት ክልሎች ውስጥ እንዲዋቀሩ ማድረግ አስፈላጊ ይመስለኛል።

በሁለተኛው ዙር ምርጫ - ከ90-110 የፖለቲካ ፓርቲዎች ይለፉ እንበል። ስለሆነም በምርጫ ውጤት 35% ያመጣ በቀጥታ ያልፋል። ከ30-34% ያገኙት ከሌሎች ጋር በመዋሃድ ለሃገራዊ ምርጫ ይዘጋጃሉ። ስለሆነም 20-25 ፓርቲዎች ለሶስተኛ ዙር ምርጫ ይዘጋጃሉ።

## የክፍለ አገራት ምርጫ

ለሶስተኛው ዙር ምርጫ - ባጠቃላይ 20-25 የተዋሃዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይለፉ እንበል። አንድ ክፍለ አገር ውስጥ 5 ሚሊየን መራጭ ወይም 5000 የምርጫ ጣቢያዎች አሉ እንበል። በአንድ ክፍለ አገር ውስጥ በአማካይ 3 ወይም 4 የፖለቲካ ፓርቲዎች ይወዳደሩ እንበል። ክፍለ አገር በአራት ማዕዘን ቅርፅ (ብርቱካናማው ቀለም) ይመሰላሉ። በአጠቃላይ ስምንት (8) ክፍለ አገራት ይኖራሉ።




ስምንት (8) ክፍለ አገራት የሚያርፉት ቦታዎች አሁን ባለው አንድ “ክልል” ውስጥ ብቻ መሆን አይገባውም። ማለትም ለምሳሌ የአማራ “ክልል” ከሚዋሰኑት “ክልሎች” ጋር በሰሜንም፤ በምስራቅም፤ በደቡብም፤ በምዕራቡም ማዛመድ ያስፈልጋል።

ስለሆነም በምርጫ ውጤት 45% ያመጣ በቀጥታ ያልፋል። እዚህ ደረጃ ላይ መዋሃድ አይፈቀድም። ስለሆነም አራት (4) ወይም አምስት (5) ፓርቲዎች ብቻ ወደ ፓርላማ ይገባሉ ማለት ነው።

| | Elections | Polling Stations - PS | Population | Election group per PS | Reg. Required | No of Parties | No. of PS | Average No of Parties | Min %-age 1 | Max %-age 2 | Average No of Parties |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 40,000 | 1,000 | | 1,000 | 300 | | | | | 300 |
| 1st | Locals | | 50,000 | 800 | | | 50 | 3 | 25% | 35% | 100 |
| 2nd | Counties | | 1,000,000 | 40 | | | 20 | | 30% | 40% | 30 |
| 3rd | Provinces | | 5,000,000 | 8 | | | 5 | | 30% | 50% | 5 |

በዚህ ሁኔታ ከተመዘገቡት ከ250 - 300 የፖለቲካ ፓርቲዎች 4 ወይም 5 የፖለቲካ ፓርቲዎች አዲሱ ፓርላማ ይገባሉ። ይህ ዓይነት የምርጫ ውድድር ማለትም የሶስት ዙር ምርጫ የሚደረገው አንድ ጊዜ ብቻ ነው።

*ወደ ህዝቡ የመውረድ ጥቅሙ ምንድነው?*

የፖለቲካ ፓርቲዎች ህዝቡ ውስጥ ገብተው የመጀመሩ ጥቅሙ ምንድነው?

1) አዳዲስና ተደብቀው ያሉትን መሪዎች ብቅ ብቅ እንዲሉ ወይም እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡
2) የዲሞክራሲ ልምድ የሚዳብረው የፖለቲካ ፓርቲዎች ከህዝቡ ውስጥ ገብተው በህዝቡ ድምፅ ሲፈተን ብቻ ነው።
3) የሴራ ፖለቲካችንን ይቀንሰዋል። ከዚህም በተጨማሪ የ1 ለ 5 የፖለቲካ መዋቅርን ይደረማምሰዋል።
4) ወጣቶች በኃላፊነትና በመርህ በፖለቲካው ውስጥ እንዲንቀሳቀሱ ይረዳል።

*ወደ ህዝቡ ያለመውረድ ጉዳቱ ምንድነው?*

1) የዲሞክራሲ ባህል እንዳይኖረንና በስልጣን ያሉት ግለሰቦች የፈለጉትን "በህዝብ" ስም እንዲሰሩ መንገድ ይከፍታል። እስካሁን እንደሚደረገው ማለት ነው።
2) የ"ሴራ ፖለቲካችን" ተጠናክሮ እንዲቀጥል ያደርጋል።
3) በአንድ አገር ውስጥ "ትናንሽ የጎሳ መንግስታትን" ፈጥሮ መሻኮቱን እንቀጥላል።
4) ብሎም ህወሃት በጠዋቱ እንደደገሰልን "ኢትዮጵያ" የምትባል አገርን እስከማጣት እንደርሳለን የሚል ግምት አለኝ።

*ምርጫው ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?*

በተጨማሪም ከሌሎች አገራቶች ልምድ (በተለይም ሃንጋሪ) እንዳየነው ይህን ዓይነት <u>የሶስት ዙር</u> ምርጫ ለማካሄድ <u>ከስድስት (6) እስከ ዘጠኝ (9) ወር ብቻ</u> ይፈጃል። አማካይ የዙር ምርጫ እስከ 3 ወር ይፈጃል።

*የገንዘብ ምንጭ*

ይህንን ዓይነት ምርጫ ለማካሄድ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ዲሞክራሲ የሚመጣው ማንኛውም ተፅህኖ የሌለበት የገንዘብ ድጋፍ ሲደረግ ነውና በዚህም መሰረት <u>በግምት</u> ባጠቃላይ <u>2 ሚሊየን ብር ወይም 70 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ነው።</u> የዚህ ሂሳብ ግምት ሲወጣ መንግስት በየወረዳውና በየአውራጃው ለፓርቲዎች <u>ጊዜያዊ ቢሮዎችን ያዘጋጃል፣ እንዲሁም የዜና ማሰራጫ መድረኮችን እኩል ጊዜ ይሰጣል</u> የሚለውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን እዚህ ላይ ወጪ ብዬ የያዝኩት መሰረታዊ ለሆኑ የአንድ ወይም ሁለት ጊዜ የስብሰባ ወጪዎች (የኢት. ብር 3,000.00 / በፓርቲ) ብቻ ነው። ለምሳሌ በመጀመሪያ ዙር 300 ፓርቲዎች ቢመሰረቱ አጠቃላይ ወጪው የኢት ብር 900,000.00 ይሆናል። በሁለተኛው ዙር 100 ፓርቲዎች ቢኖሩ (የኢት. ብር 5,000.00 / በፓርቲ) የኢት. ብር 500,000.00 ይሆናል። ለሶስተኛ ዙር ያለፉት ደግሞ 30 ፓርቲዎች (የኢት. ብር 20,000.00 / በፓርቲ) የኢት. ብር 600,000.00 ይደርሳቸዋል ማለት ነው። ለዚህ <u>የገንዘብ ምንጩ</u> ደግሞ ዲሞክራሲን አገሩ ውስጥ እንዲኖርለት የሚናፍቀው <u>በውጪ አገር የሚገኘው ኢትዮጵያዊ</u> ወይም በተለምዶ አጠራር "ዲያስፖራው" ቢሆን ይመረጣል።

| | Elections | Polling Stations - PS | Population | Election group per PS | Average No of Parties | Timeline | Ave Cost in Birr | Ave Total Cost in Birr | Average In USD |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 40,000 | 1,000 | | 300 | | 3,000 | 900,000 | 30,000 |
| 1st | Locals | | 50,000 | 800 | 100 | 2-3 months | 5,000 | 500,000 | 17,000 |
| | | | | | | | | | |
| 2nd | Counties | | 1,000,000 | 40 | 30 | 1-2 months | 20,000 | 600,000 | 20,000 |
| | | | | | | | | | |
| 3rd | Provinces | | 5,000,000 | 8 | 5 | 1-2 months | | - | - |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | 2,000,000 | 67,000 |

ምክንያቱም የገንዘቡ ምንጩ ሌሎች አገሮች ከሆኑ የ"ጥቅም ግጭት" እንዳይፈጥር ያሰጋልና። የውጪ አገራቶች ገንዘብ ሲሰጡ ከዚያም ተከትሎ የሚመጣ ችግር እንዳለ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

## ማጠቃለያ

በአሁኑ ጊዜ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የሕብረተሰቡን ትኩሳት ገብቶት ከላይ እንደጠቀስኩት የራሱን የፖለቲካ ፖሊሲ ወደ ህዝብ እስከሚያወርድ ድረስ የሰላማዊ ትግል ማድረግና በየቦታውም በፖለቲካ ፓርቲ መደራጀት ጠቃሚ መስሎ ይታየኛል። ታዲያ ህዝቡ በፖለቲካ ፓርቲዎች ራሱን ሲያዋቅር ደግሞ ሁለቱን መሰረታዊ ነገሮችን ማለትም የአባላት ፊርማ ማሰባሰብና ግልፅ የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም ማዘጋጀት ግድ ይለዋል። የፖለቲካ ፕሮግራሙ የሚያሳየው ፓርቲው ቢመረጥ ኢትዮጵያን እንዴት ማስተዳደር እንደሚገባው ሲሆን የፖለቲካ ፕሮግራሙ የሚያጠቃልለው "... በአስተዳደር፣ በምጣኔ ሃብት፣ በእርሻ፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በኢንዱስትሪ፣ በንግዱ፣ በመገናኛ ዘርፍ፡ ወዘተ" ፓርቲው ያለውን አቋም የማሳየት ግዴታ ይኖርበታል። የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ አገር ውስጥ መበራከት ደግሞ እንደ ዲሞክራሲያዊ ልምምድ፣ ጠንካራ ሃሳብ እንዲያሸንፍ እንጂ እንደ ድክመት መወሰድ አይገባውም የሚል ሃሳብ አለኝ። የፖለቲካ ፓርቲዎች ውህደት የሚፈጠርበትን መንገድ / መፍትሄው ማዘጋጀት ያለበት መንግስት ስለሆነ ይህንን መፍትሄ እንዲያመጣ መጎትጎት ደግሞ የህዝቡ ሃላፊነት ነው።

Revised - April 2019

ጥያቄ ወይም አስተያየት ካሎት በሚከተለው ኢ-ሜይል ይጠቀሙ። tayele@yahoo.com

[1] የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ ከውድ አገሩ ኢትዮጵያ ለትምህርት የወጣው በ1987 ዓ.ም. ሲሆን ትምህርቱንም የጨረሰው ሃንጋሪ ውስጥ ነው። በምጣኔ ሃብት (Economics) የዶክትሬት ዲግሪ ይዟል።

በ1990 ወይም 1991 ዓ.ም. የደቡብ አፍሪካ የኤንሲ ተወካዮች ሃንጋሪ መጥተው የለውጥ ሂደቱን በአንክሮ ሲከታተሉ እንደነበርና ደቡብ አፍሪካውያን ይህንን ለውጥ እንደ ሞዴልነት ተጠቅመውበታል። መረጃዎች እንደሚያሳዩት በወቅቱ ወደ 8 ሺህ የሚጠጉ ሃንጋሪያውያንና 6 ሺህ የሚጠጉ ቼኮዘሎቫኪያንስ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ነበሩ።

[2] Revolutionary Democracy - Source: https://www.reddit.com/r/RevDem/comments/55cq47/what_is_revolutionary_democracy/

[3] Democracy: Advantages and Disadvantages of Democracy Category: Essays, Paragraphs and Articles By Pawan Srivastav - Source: https://www.importantindia.com/15738/advantages-and-disadvantages-of-democracy/

[4] African National Congress Meets Estern Europe — The relevance of the Hungarian constitutional experiance

[5] Gabor Toka: Hungary

[6] www.wikipedia.com — Hungary

[7] In Hungary, there are 13 recognized minorities including Germans, Slovaks, Croats, Romanians, Poles, Bulgarians, Greeks, Armenians, Ruthenians, Serbs, Slovenes and Ukrainians. Roma represent the largest minority population, generally estimated between 200,000 and 600,000

[8] Source: https://www.importantindia.com/16621/functions-of-political-parties-in-democracy/